This VIS translation is out of date. When you give your patient this translation, also give them the up-to-date English version of it.
To get both, and to find out what was updated, go to www.immunize.org/vis

# ኩፍኝ ፡ ጆሮ ደግፍ ፡ እና ሩቤላ ክትባት (ኤምኤምአር) (MMR)

## ማወቅ የሚያስፈልግዎት ነገር

## 1 ለምን መከተብ ያስፈልጋል?

ኩፍኝ ፡ ጆሮ ደግፍ ፡ እና ሩቤላ ከፉ በሽታዎች ናቸው።

**ኩፍኝ**
የኩፍኝ ቫይረስ የሚያመጣው-
• ችፍታ • ማስላት • ማናፈጥ • ዓይን ማቃጠል • ትኩሳት
ሊያስከትል የሚችለው ፡ • የጆሮ መታመም • የብርድ በሽታ
• የመጣል በሽታ (ማንቀጥቀጥ እና ማፍጠጥ) • የአንጎል መጎዳት
• ሞት

**ጆሮ ደግፍ**
የጆሮ ደግፍ ቫይረስ የሚያመጣው-
• ትኩሳት • የራስ ምታት • የዕጢዎች ማበጥ
ሊያስከትል የሚችለው ፡
• የጆሮ መደንቆር • ሜንነጃይትስ (የአንጎልና የአከርካሪ አጥንት ሽፋን በበሽታ መለከፍ) • የወንድ ዘር ፍሬን ወይም ማህጸንን (ኦቫሪ) የሚያም እብጠት • አልፎ አልፎ ፡ ሞት

**ሩቤላ (የጀርመን ኩፍኝ)**
ሩቤላ የሚያመጣው-
• ችፍታ • መለስተኛ ትኩሳት ፡ እና • አርተራይተስ (የአጥንት በሽታ) (ብዙውን ጊዜ በሴቶች ላይ)

**ሩቤላ**
አንድ ሴት በእርግዝናዋ ወቅት ሩቤላ ከያዛት ሊያስወርዳት ወይም ልጇ ከፉ የአካል መታጎል (በርዝ ድፌክት) ኖሮት ሊወለድ ይችላል።

በሽታው በያዛቸው ሰዎች አጠገብ በመሆን እርሶና ልጅዎን በሽታዎቹ ሊይዟችሁ ይችላሉ። ከሰው ወደ ሰው በአየር ይተላለፋሉ።

የኩፍኝ ፡ ጆሮ ደግፍ ፡ እና ሩቤላ (ኤምኤምአር) (MMR) ክትባት ይህን ሊያስወግድ ይችላል።

አብዛኞቹ የኤምኤምአር (MMR) መርፌ የሚወጉ ልጆች በሽታው አይይዛቸውም። ከትባቱን ብናቆም ተጨማሪ ብዙ ልጆች በሽታው ይይዛቸዋል።

## 2 የኤምኤምአር (MMR) ክትባት መከተብ ያለበት ማነኛ መቼ ነው?

ልጆች 2 መርፌ የኤምኤምአር (MMR) ክትባት መወጋት

✓ ያስፈልጋቸዋል። የመጀመሪያው ከ12 – 15 ወር ዕድሜ ላይ እና
✓ ሁለተኛው በ4 – 6 ዓመት ዕድሜ ላይ።

እዚህ የሚታዘዙት ዕድሜዎች ናቸው። ነገር ግን የመጀመሪያውን ከተወጉ ቢያንስ 28 ቀናት እስከሆናቸው ድረስ ልጆች ሁለተኛውን መርፌ በማንኛውም ዕድሜ ላይ ሊወጉ ይችላሉ።

**አንዳንድ አዋቂ ሰዎችም የኤምኤምአር (MMR) ክትባት መከተብ ያስፈልጋቸዋል ፡**
ባጠቃላይ 18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ የሆነው ከ1956 በኋላ የተወለደ ማንኛውም ሰው ቢያንስ አንድ የኤምኤምአር (MMR) መርፌ መወጋት ያስፈልገዋል ፡ ከትባቱን ተከትበው እንደነበር ወይም በሽታው ይዟቸው እንደነበር ማስረዳት የሚችሉ ከሆኑ በስተቀር።

ለተጨማሪ መረጃ ሐኪምዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ።

እንደ ሌሎች ከትባቶች የኤምኤምአር (MMR) ክትባት ባንድ ወቅት ሊሰጥ ይችላል።

## 3 አንዳንድ ሰዎች የኤምኤምአር (MMR) መወጋት የለባቸውም ወይም መቆየት አለባቸው።

• ለጀላቲን ፡ አንቲባዮቲክስ ኒዮማሲን፣ ወይም ከዚህ በፊት ለተወጉት የኤምኤምአር (MMR) መርፌ ለሕይወት የሚያሰጋ አለርጂ ኖሯቸው የሚያውቁ ሰዎች የኤምኤምአር (MMR) ክትባት መጋት የለባቸውም።

• መርፌው በታዘዘላቸው ወቅት በመጠኑ ወይም በጽኑ የታመሙ ማናቸውም ሰዎች የኤምኤምአር (MMR) ክትባት ከመወጋታቸው በፊት ሕመማቸው እስኪሻላቸው ጊዜ ድረስ መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል።

• እርጉዝ ሴቶች የኤምኤምአር (MMR) ክትባት ለመከተብ ልጅ ከወለዱ በኋላ እስካለው ጊዜ ድረስ መጠብቅ ያስፈልጋቸዋል። ሴቶች የኤምኤምአር (MMR) ክትባት ከተከተቡ በኋላ 4 ሳምንታት ውስጥ ማርገዝ የለባቸውም።

• አንዳንድ ሰዎች የኤምኤምአር (MMR) ክትባት መከተብ ያስፈልጋቸው እንደሆነ ሐኪማቸውን ማማከር ያስፈልጋቸዋል ፡ የሚከተሉትንም ጨምሮ ፡
  - (ኤችአይቪ/ኤድስ) HIV/AIDS ወይም የሰውነት በተፈጥሮ ከበሽታ መከላከያን የሚያውክ በሽታ ያለባቸው ሰዎች
  - የሰውነት በተፈጥሮ ከበሽታ መከላከያን በሚነካ መድሐኒት የሚታከም ሰው ፡ እንደ ስቴሮይድስ ያሉትን ለ2 ሳምንት ወይም በበለጠ ጊዜ ፡ የኤምኤምአር (MMR) ክትባት መከተብ ያስፈልጋቸው እንደሆነ ሐኪማቸውን ማማከር ያስፈልጋቸዋል።
  - ማንኛውም ዓይነት ካንሰር ያለበት
  - በኤክስ –ሬይ ወይም በመድሐኒት የካንሰር ሕክምና የሚያደርጉ
  - አነስተኛ የፕሌይትሊት መጠን (የደም በሽታ) ኖሯቸው የሚያውቁ

- በቅርብ ጊዜ ውስጥ ደም የተሰጣቸው ወይም ሌሎች የደም ውጤቶች የተሰጣቸው ሰዎች መቼ የኤምኤምአር (MMR) ክትባት መከተብ እንዳለባቸው ሐኪማቸውን መጠየቅ ያስፈልጋቸዋል።

ለተጨማሪ መረጃ ሐኪምዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ።

## 4 ከ ኤምኤምአር (MMR) ክትባት የሚመጡ አደጋዎች ምንድን ናቸው?

እንደ ማንኛውም መድሐኒት መርፌ ኃይለኛ አለርጂን የመሰለ ጽኑ ችግርን ማስከተል ይችላል። የኤምኤምአር (MMR) ክትባት ጽኑ ጉዳትን ወይም ሞትን የማምጣቱ አደጋ በጣም ትንሽ ነው።

የኤምኤምአር (MMR) ክትባት መከተቡ ከእነዚህ ከሦስቱ በሽታዎች ውስጥ ባንዱ በመያዝ ካለው አደጋ በጣም የተሻለ ነው።

አባዛኞቹ የኤምኤምአር (MMR) ክትባት የሚከተቡ ሰዎች በክትባቱ ምንም ችግሮች የሉባቸውም።

### መለስተኛ ችግሮች ፡

- ትኩሳት (1 ሰው ከ 6 ድረስ)
- መለስተኛ ችፍታ (1 ሰው ከ20 ያህል)
- በጉንጭ ወይም በአንገት ውስጥ ያሉ ዕጢዎች ማበጥ (አልፎ አልፎ)

እነዚህ ችግሮች ከተከሰቱ ፡ ብዙውን ጊዜ ከመርፌው በኋላ ከ7-12 ቀናት ውስጥ ነው። ከሁለተኛው መርፌ በኋላ አልፎ አልፎ ይሆናሉ።

### መጠነኛ ችግሮች ፡

- በትኩሳት የመጣ መጣል (ማንቀጥቀጥ ወይም ማፍጠጥ) (1 ከ 3,000 ያህል)
- በመጋጠሚያዎች ላይ ጊዜያዊ ሕመምና ድርቅ ማለት ፡ ብዙውን ጊዜ በጎረምሳ/ኮረዳ ወይም በአዋቂ ሴቶች ላይ (1 ከ4 ድረስ)
- ጊዜያዊ አነስተኛ የፕሌይትሌት ብዛት ፡ ይህም የደም መፍሰስ ሁኔታን ያመጣል (1 ከ 30,000 መፌዎች ያህል)

### ጽኑ ችግሮች (በጣም አልፎ አልፎ የሆነ)

- ኃይለኛ የአለርጂ ሁኔታ (1 ከሚሊዮን መርፌ ባነሰ)
- ሌሎች ብዙዎች ችግሮች አንድ ልጅ የኤምኤምአር (MMR) ክትባት ከተከተበ በኋላ እንደሚከሰቱ ታውቋል። ግን ይህ የሚሆነው በጣም አልፎ አልፎ ነው ፡ የበሽታው አዋቂዎች የችግሮቹ መንስኤ ከትባቱ ይሆን ወይም አይሆን እርግጠኛ አይደሉም። እነሱም የሚያጠቃልሉት፡
  - የጆሮ መደንቆር
  - የረጅም ጊዜ የመጣል ሁኔታ፡ ኮማ ፡ ወይም የቀነሰ የአእምሮ ንቃት
  - ለዘላለም የአንጎል መጎዳት

## 5 መጠነኛ ወይም ኃይለኛ የመርፌ መጣላት (ሪአክሽን) ቢኖርስ?

### ምን ምልክትን ማየት ያስፈልገኛል?

ያልተለመዱ ሁኔታዎች ምልክቶች ፡ እንደ ጽኑ አለርጂ፡ ከፍተኛ ትኩሳት፡ ወይም የባህርይ ለውጥ የመሰሉ ሁኔታዎች።

የጽኑ አለርጂ ምልክቶች የሚያጠቃልሉት ከመርፌው በኋላ ከጥቂት ደቂቃዎች እስከ ጥቂት ሰዓቶች ውስጥ ባለው ጊዜ ውስጥ የትንፋሽ ማጠር፡ የድምጽ መጎርናት ወይም ማቃተት፡ የቆዳ መጉረብረብ፡ የቆዳ መገርጣት፡ መድከም ፡ የልብ ቶሎ ቶሎ መምታት፡ ወይም የማዞር ምልክቶች። ከፍተኛ ትኩሳት ወይም መጣል ፡ ከተከሰተ ፡ ከመርፌው በኋላ ከ1-2 ሳምንታት ውስጥ ይሆናል።

### ምን ማድረግ ያስፈልገኛል?

- ለሐኪም ይደውሉ፡ ወይም ወደ ሐኪም የሚወስድዎትን ሰው በአስቸኳይ ይጥሩ።
- ለሐኪምዎ ምን እንደሆነ ፡ የሆነበትን ቀንና ሰዓት ፡ እንዲሁም መርፌውን መቼ እንደተወጉ ይንገሩ።
- የ'ቫክሲን አድቨርስ ኢቨንት ሪፖርቲንግ ሲስተም' (ቪኤኢአርኤስ) (VAERS) ቅጽ በመሙላት ስለ አለርጂው ሐኪምዎን ፡ ነርስዎን ፡ ወይም የጤና ክፍልን ይጠይቁ። ወይም ይህን ሪፖርት በ በቪኤኢአርኤስ (VAERS) ዌብሳይት www.vaers.org በኩል ወይም 1-800-822-7967 በመደወል ሊያስገቡ ይችላሉ። *ቪኤኢአርኤስ (VAERS) የሕክምና ምክር አይሰጥም።*

## 6 ብሔራዊ የክትባት ጉዳት መካሻ ፕሮግራም (The National Vaccine Injury Compensation Program)

አልፎ አልፎ እርሶ ወይም ልጅዎ ከክትባት ብርቱ አለርጂ በሚኖርባችሁ ጊዜ ለተጎዳው ሰው ሕክምና ለመስጠት ለክፍያው ሊረዳ የሚችል የፌደራል ፕሮግራም ተቋቁሟል።

ስለ ብሔራዊ የክትባት ጉዳት መካሻ ፕሮግራም (The National Vaccine Injury Compensation Program) ዝርዝር **1-800-338-2382** ይደውሉ ወይም የፕሮግራሙን ዌብሳይት www.hrsa.gov/osp/vicp ይጎብኙ።

## 7 በተጨማሪ መማር የምችለው እንዴት ነው?

- ሐኪምዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ። ስለ ክትባቱ ዝርዝር መረጃ ጹሑፍ ይሰጡዎታል ወይም ስለ ሌሎች የመረጃ ምንጮች ሃሳብ ይሰጡዎታል።
- ለአካባቢዎ ወይም ለስቴቱ ጤና ክፍል የክትባት ፕሮግራም ይደውሉ።
- ለ Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ይደውሉ፡
  - **1-800-232-4636 (1-800- CDC-INFO)** ይደውሉ ወይም
  - የ National Immunization Program ዌብሳይት www.cdc.gov/nip ይጎብኙ።

CDC

U.S. DEPARTMENT OF HEALTH & HUMAN SERVICES
Centers for Disease Control and Prevention
National Immunization Program

Vaccine Information Statement
MMR (1/15/03) - Amharic 42 U.S.C. § 300aa-26

Translation provided by Healthy Roads Media